# የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለስልጣን

## የብሔራዊ ሎጂስቲክስ ም/ቤትና የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት አጭር መግለጫ

1. መግቢያ 3
2. የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ም/ቤትና ጽ/ቤት ዳራ ........ 4
2.1 የብሔራዊ ሎጂስቲክስ ም/ቤቱ አመሰራረት ........ 4
2.2 የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ም/ቤቱ ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት ........ 4
2.3 የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት አመሰራረት ........ 5
2.4 የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት ዓላማ፣ ራዕይ፤ ተልዕኮና ተግባራት ........ 6
2.4.1 ዓላማ ........ 6
2.4.2 ራዕይ ........ 6
2.4.3 ተልዕኮ ........ 6
2.4.4 የጽ/ቤቱ ዋና ዋና ተግባራት ........ 6
2.4.5 የትግበራ ቡድኑ ኃላፊነትና ተግባር ........ 8

## 1. መግቢያ

የሀገራችን የውጭ እና የሀገር ውስጥ ንግድ  በመጠንና በዓይነት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የንግድ ሎጅስቲክሱን ውጤታማ ለማድረግ እና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ምርታማነት ለማሳደግ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ መከናወን ካለባቸው ቁልፍ ተግባራት ውስጥ ዋናው በጊዜ፤ በወጪ፤ በተዓማኒነትና በጥራት ያደገ  የሎጅስቲክስ አገልግሎት እውን ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ሎጅስቲክስ አገልግሎት በዋና ዋና የሎጅስቲክስ መለኪያዎች ከመሰል ሀገሮች ጋር ሲወዳደር በእጅጉ ወደ ኋላ የቀረ መሆኑ ከታወቀ ብዙ ጊዜ አስቆጥሯል፡፡  ወደ ኋላ መቅረቱ ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱን ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርግ መሆኑና አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገታችንን የሚገታ በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው ነው፡፡

ከዚህ አጻር በሀገር ደረጃ የተፈጠረውን አጠቃላይ የመንግስት አሰራር ለውጥ ተከትሎ  ለረጅም ዓመታት ሲንከባለሉ የነበሩ በርካታ ቁልፍ ጉዳዮች ውሳኔ አግኝተዋል፡፡

በተለይም ለብዙ ጊዜ ሲደከምበት የነበረው የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂ በኢፌዴሪ የሚንስትሮች ም/ቤት ጸድቆ ከ2013 በጀት አመት መጀመሪያ ጀምሮ ሙሉ ለሙሉ ወደ ትግበራ ተሸጋግሯል፡፡ የትራንስፖርት ፖሊሲ እና የሎጅስቲክስ ዘርፍ ፖሊሲ በተመሳሳይ መልኩ በሚኒስትሮች ም/ቤት ጸድቀው በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂውን ለማስተግበር የሚያስችል አደረጃጀት የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ም/ቤትና የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት ተቋቁሞ የተጣለባቸውን አገራዊ ሀላፊነት በመወጣት ላይ ናቸው፡፡

## 2. የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ም/ቤትና ጽ/ቤት ዳራ

### 2.1 የብሔራዊ ሎጂስቲክስ ም/ቤቱ አመሰራረት

የሎጅስቲክስ ዘርፍ ፖሊሲና የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂን ተግባራዊ ለማድረግ፤ የሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ትራንስፎርም ለማድረግና እንደሀገር በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነታችንን ለማረጋገጥ ብሎም በአስተማማኝ ደረጃ ለማስቀጠል፤ በሎጅስቲክስ ዘርፍ ቁልፍ ሚና ያላቸው ተቋማት መቀናጀት ብቻ ሳይሆን ሎጅስቲክስ ነክ የሆኑ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች የሚመሩ በተለያየ ደረጃ የተዋቀሩ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን በበላይነት የመምራት፤ በጋራ ማቀድ፣ በጋራ መገምገም፣ የሎጅስቲክስ ሥራዎችን እንደየድርሻቸው ቆርሰው በመውሰድ መተግበርን ይጠይቃል፡፡ ከዚህም ባለፈ ይህን ትልቅ ኃላፊነት ለማቀናጀት ከፍተኛ ውሣኔ የሚሹ ጉዳዮችን በወቅቱ ለመወሰንና ለማስፈጸም የከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች አመራር (High Level Leadership) ወሣኝ ነው፡፡ ለዚህም ትልቁ ዓምድ (pillar) በብሄራዊ ደረጃ በሎጅስቲክስ ሥርዓት ቁልፍ ሚና ያላቸው የሚኒስቴር መ/ቤቶችና ተቋማትን ያካተተ በከፍተኛ ኃላፊ የሚመራ፣ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያለው ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ም/ቤት በህግ ተቋቁሞ ስራውን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

### 2.2 የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ም/ቤቱ ዋና ዋና ሥልጣንና ተግባራት

የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ም/ቤት ስልጣንና ተግባራቱ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ በዝርዝር የተደነገገ ሲሆን ጠቅለል ብሎ ሲታይ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራትን የያዘ ነው፡፡

ይኸውም:-

- ✓ የብሔራዊ ሎጀስቲክስ ስትራቴጂ ውጤታማ ሆኖ እንዲተገበር የሚያስችል አመራር የመስጠት፤ የመወሰን እና የማስፈጸም፣
- ✓ በአገራችን የሎጀስቲክስ ሂደት ውስጥ አግባብ ባላቸው አካላት ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስቸል ፖሊሲ የማስፈጸም፣

- ✓ የአገሪቱን የሎጀስቲክስ አፈፃፀም ላይ ማነቆ የሚሆኑ ፖሊሲዎች፣ ህጎችና አሠራሮችን እንዲለዩ የማድረግ፤ በሚመለከታቸው ተቋማት እንዲሻሻሉ ውሳኔ የማስተላለፍ፣
- ✓ የአገሪቷን የሎጀስቲክስ ክዋኔ በገለልተኛ የሎጀስቲክስ ባለሙያዎች ወይም በባለሞያዎች ማኀበር የክዋኔ ኦዲት የማስደረግ፤ በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት እርምጃ የመውሰድ፣
- ✓ የክልል እና የከተሞች የሎጀስቲክስ ምክር ቤት እንዲቋቋም አቅጣጫ እና አመራር የመስጠት፣
- ✓ የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤቱን የተሟላ አቅም እንዲኖረው አድርጎ የማደራጀት፣
- ✓ አስፈላጊነታቸው የታመነባቸው ሌሎች አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ የማድረግ እና የም/ቤት አባላትን ቁጥር የመጨመር ወይም የመቀነስ፤ ስልጣን አለው፡፡

## 2.3 የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት አመሰራረት

የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት በብሄራዊ የሎጅስቲክስ ም/ቤት የሚወስኑ ጥናቶች፣ የፖሊሲ ሃሣቦች፣ ሪፖርቶች፣ ፕሮግራሞችና መሰል ሥርዓቱን ትራንሰፎርም ለማድረግ ወሣኝ የሆኑ ፕሮፖዛሎችን የሚያቀርብ ነው፡፡ ም/ቤቱም ሆነ መንግስት የሎጅስቲክስ ዘርፉን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሣኔዎች በተሳሳተ መረጃ እንዳይሆን በትክክለኛ መረጃና በቂ ትንታኔ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ኃላፊነት አለበት፡፡ በሎጅስቲክስ ስትራቴጂው ውስጥ ያሉት የመፍትሄ ሃሳቦችን (Interventions) ወደ ፕሮግራም የመለወጥ፣ የትግበራ መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ ትግበራውን በተሟላ መልኩ መከታተልና በዘርፉ የሚገኙት ተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ አካላትን በማቀናጀት የስትራተጂውን ትግበራ የተሟላ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህ ጽ/ቤት በሂደት እየተጠናከረ የሚሄድ ሆኖ በሎጅስቲክስ/ሰኘላይ ቼይን ዘርፍ ከፍተኛ ትምህርት ያላቸው (Academia) ከኢንዱስትሪው በቂ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ያካተተ እንዲሆን ተደርጎ ለማደራጀት ተሞክሯል፡፡

## 2.4 የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት ዓላማ፣ ራዕይ፤ ተልዕኮና ተግባራት

### 2.4.1 ዓላማ

የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት ዋና ዓላማ የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂውን በመተግበር የሎጂስቲክስ ዘርፉን ትራንስፎርም ማድረግ ነው፡፡

### 2.4.2 ራዕይ

በ2020 ዓ.ም መጨረሻ የሎጅስቲክስ ሥርዓታችን የሀገራችንን የንግድና የኢንቨስትመንት ዕድገት በማሳለጥ ከአፍሪካ ቀዳሚ ሆኖ ማየት፡፡

### 2.4.3 ተልዕኮ

የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት ተልዕኮ የሎጅስቲክስ የማስፈጸም አቅምን በመገንባት፣ በዘርፉ ቁልፍ ሚና ያላቸውን ተቋማት በማስተባበርና በማቀናጀት፣ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ፤ ችግር ፈቺ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽና በመተግበር የሀገራችን ሎጅስቲክስ ሥርዓት ትራንስፎርም ማድረግ ነው፡፡

### 2.4.4 የጽ/ቤቱ ዋና ዋና ተግባራት

የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት ስልጣንና ተግባራቱ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ በዝርዝር የተደነገገ ሲሆን ጠቅለል ብሎ ሲታይ የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራትን የያዘ ነው፡፡

እነሱም፡-

- ✓ በዋናነት የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ የማገልገል፣
- ✓ የአገራችን ሎጂስቲክስ አፈጻጸም ማነቆዎችን በጥናት የሚፈቱበትን ሥልት የመንደፍ፤ አፈጻጸማቸውን የመከታተል፣
- ✓ በብሔራዊ ሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ውስጥ የተገለጹ የመፍትሄ ሐሣቦችን ወደ ፕሮግራም፣ ወደ ፕሮጀክት እንዲሁም ወደ አሠራር የመለወጥ፤ አፈጻጸማቸውን የመከታተል፣

- ✓ በስትራቴጂው ትግበራ ጊዜ የሚያጋጥሙ የፖሊሲ፣ የህግ፣ የአሠራር ፣ የመሠረተ-ልማት ማነቆዎችን በጥናት በመለየት የመፍትሄ ሃሣብ ለም/ቤቱ የማቅረብ፤ የማስወሰንና ትግበራውን የመከታተል፣
- ✓ በም/ቤቱ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በሚመለከታቸው አካላት እንዲፈሙ የመደገፍና አፈጻጸማቸውን የመከታተል፣
- ✓ የአገሪቷን ሎጂስቲክስ በተመለከተ በተለያየ የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋማት የሚጠኑ ጥናቶችን በማዕከላዊነት የመከታተል፤ ድጋፍ የመስጠት እንዲሁም የተጠኑ ጥናቶችን በመረጃ ማዕከልነት የመያዝና ለሚመለከተው የማሰራጨት፣
- ✓ የሎጅስቲክስ ዘርፍን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከቱ አዋጆች፤ ደንቦች እና መመሪያዎች አግባብነታቸውን የመፈተሽ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማሻሻያ መነሻ ሃሣብ ለም/ቤቱ የማቅረብ፣
- ✓ በሎጅስቲክስ ዘርፍ ሀገሪቱን አፈጻጸም የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች ሲወጡ መረጃዎችን በመመርመር በመረጃ ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ ሪፖርት የማዘጋጀት እና ለም/ቤቱ የማቅረብ፣
- ✓ የትራንዚት ኮሪደር አጠቃቀም ላይ የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን በመከታተልና በመለየት የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ የመፍትሄ ምክረ-ሐሣብ ለም/ቤቱ የማቅረብ፣ ትግበራቸውን የመከታተል፣
- ✓ የጽ/ቤቱን ሰራተኞች ደሞዝ፤ የስራ ማስኬጃ በጀት እና ሌሎችም በዋናነት ደግሞ የስትራቴጂው ማስፈጸሚያ በጀት ከሚመለከተቻው ዓለም አቀፍ አበዳሪዎች፤ ደጋፊዎች እና በጎ አድራጊዎች ገንዘብ ለማግኘት የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፎ በም/ቤቱ አጸድቆ ስራ ላይ የማዋል፤ ኃላፊነቶች አሉት፡፡

### 2.4.5 የትግበራ ቡድኑ ኃላፊነትና ተግባር

የትግበራ ቡድን በሎጅስቲክስ ዘርፍ ከሚገኙ ተቋማት የተደራጀ ሲሆን ዋና ዋና ተግባራቱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ በሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት በኩል በሚቀረጹ ሎጅስቲክስ ነክ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ሂደት ውስጥ ተቋማቸውን በመወከል በንቃት የመሳተፍ፣
- ✓ የተዘጋጁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ከተቋማቸው አሰራር አንጻር በመቃኘት አስተያየትና ግብዓት የመስጠት፣
- ✓ በም/ቤቱ የጸደቁ የሎጅስቲክስ ፕሮግራሞች፤ ፕሮጀክቶችና መርሀ-ግብሮችን የድርሻቸውን በመወሰድ በተቋማቸው እንዲፈጸም የማድረግ፣
- ✓ የአፈጻጸም ሪፖርት በየጊዜው በቀጣይ በዝርዝር በሚወሰን ስርዓት መሰረት ለጽ/ቤቱ የማቅረብ፣
- ✓ በየተቋማቸው የሚከናወኑ ሎጅስቲክስ ነክ ጥናቶችና ፕሮጀክቶች ካሉ አፈጻጸማቸውን በተመለከተ ለጽ/ቤቱ በቋሚነት ሪፖርት እና የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍም ለይተው የማቅረብ፣
- ✓ በቋሚነት የተቋማቸው የሎጅስቲክስ ፎካል ፖይንት በመሆን የማገልገል፣
- ✓ ተቋሙ የሀገሪቱን ሎጅስቲክስ በማሻሻል ረገድ የድርሻውን እንዲወጣ ከጽ/ቤቱ በሚሰጣቸው ስልጠናና ድጋፍ መሰረት አስፈላጊውን የአቅም ማጎልበት ስራ በተቋማቸው የማከናወን፣
- ✓ ሌሎች በም/ቤቱ እና በጽ/ቤቱ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራትንም የማከናወን፤ ኃላፊነቶች አሏቸው፡፡